የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሶስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ - ጥር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 21
ADDIS ABABA - January 26th 2007

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፩./፲፱፻፺፱
የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ)
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ.......ገጽ ፫ሺ፭፻፹፬

## CONTENTS

*Council of Ministers Regulations No.131 .../2007*
*Tendaho Sugar Factory Establishment (Amendment )*
*Council of ministers Regulations ....... Page 3584.*

### የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፩/፲፱፻፺፱ የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ ‹‹የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፩/፲፱፻፺፱ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

፪. ማሻሻያ

የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፩፻፳፪/፲፱፻፺፰ እንደሚከተለው በዚህ ደንብ ተሻሽሏል ፡፡

፩. የደንቡ አንቀጽ ፮ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፮ ተተክቷል፤

‹‹፮ ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደለት ካፒታል ብር 2,080,000,000 (ሁለት ቢሊዮን ሰማንያ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 97,370,000 (ዘጠና ሰባት ሚሊዮን ሦስት መቶ ሰባ ሺህ ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡ ››

*Council of Ministers Regulations No.131/2007*

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO AMEND THE TENDAHO SUGAR FACTORY ESTABLISHMENT REGULATIONS*

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.471/2005 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

   These Regulations may be cited as the "Tendaho Sugar Factory Establishment (Amendment) Council of Ministers Regulations No 131/2007".

2. *Amendment*

   The Tendaho Sugar Factory Establishment Council of Ministers Regulations No. 122/2006 is hereby amended as folows.

   1. Article 6 of the Regulations is deleted and replaced by the following new Article 6:

      "6. Capital

      The Authorized capital of the Enterprise is birr 2,080,000,000 (Two Billion Eighty Million Birr ) of which birr 97,370,000 (Ninety Seven Million Three Hundred Seventy Thousand Birr) is paid up in cash and in kind."

ያንዱ ዋጋ 2.30
Unite Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ ፩
Negarit G. P.O. Box 80,001

፪. የደንቡ አንቀጽ ፱ አንቀጽ ፲ ሆኖ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፱ ተጨምሯል ፡፡

‹‹፱ <u>የመብትና ግዴታ መተላለፍ</u>

፩. የተንዳሆ እርሻ ልማት አክሲዮን ማህበር መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለድርጅቱ ተላልፈዋል፡፡

፪. የተንዳሆ እርሻ ልማት አክሲዮን ማህበር ሠራተኞች፣ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ያገኟቸው መብቶችና ጥቅሞች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ወደ ድርጅቱ ይዛወራሉ፡፡››

፫. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም፡፡

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

2. Article 9 of the Regulations is re-numbered as Article 10 and the following new Article 9 is added.

"9. *<u>Transfer of Rights and Obligations</u>*

1. The Rights and obligations of the Tendaho Argiculatural Development Share Company are hereby Transferred to the Enterprise.
2. The employees of Tendaho Agricultural Development Share Company shall, without prejudice to their rights and benefits acquired pursuant to the provisions of the labour Proclamation, be transferred to the Enterprise."

3. *<u>Effective Date</u>*

These Regulations shall enter into force as of the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 27th day of April, 2007.

*MELES ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL*

*DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ